Harla Journals

Harla Journal of Social and Behavioral Studies

Journal home page: https://journals.ddu.edu.et/index.php/HJSBS

Harla journal
of Social and Behavioral Studies

# Ejigayehu Shebabaw's 'Tinager Adwa Lyric Song' Analysis: Focus on the Nationalist Role

Daniel Mengistie

*Lecturer in Literature and Folklore, Department of English Language and Literature, College of Social Sciences and Humanities, Dire Dawa University, Email: abush1978g@gmail.com
Phone number: 251 912 186 204

## የእጅጋየሁ ሽባባዉ 'ትናገር አድዋ' የተሰኘዉ የሀገረ-ሰብ ዜማ ግጥም ትንታኔ

ዳንኤል መንግስቴ

**አኅጽሮተ-ጽሁፍ**

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ለአድዋ ከተዜሙ ዜማዎች መካከል በብዙዎቻችን ልብ ዉስጥ ያለዉ እና በሚስጥራዊ ዉብ የዜማ ግጥም የተከሸነዉን የእጅጋየሁ ሽባባዉ 'ትናገር አድዋ' የተሰኘዉ የሀገረ-ሰብ ዜማ ግጥም ትንታኔ መስጠት ነዉ፡፡ በመሆኑም የዘፈኑን ግጥም ዘርፈ ብዙ እሳቤዎች ያሉት እና የረቀቀ ማሕበራዊ ፋይዳ አለዉ፡፡ የጽሁፍ እይታዉ በትኩረት ለማሳየት የሞከረዉ አርቲስት እጅጋየሁ ሽባባዉ የሀገር ፍቅርን በሙዚቃ ፍልስፍና እንዴት አድዋን በክሰተ ምስል ማሳየት እንደሚቻል በሚገባ ያሳየናል፡፡ ኢትዮጵያ የአርበኞች ትዕምርታዊ ዉጤት እንደሆነች በትልቅ ትኩረት እንድንሰጥ መንገድ ይከፍታልናል፡፡ የሀገሪቱ ታሪካዊና ተፈጥሮዊና ቅርሶች እንዲሁም ሀገራቸዉን ለመጠበቅ የተከፈለዉን የሀገር ፍቅር ስሜት በአርቲስቷ በዜማ ግጥሞቿ ላይ በበሳል እይታ ተገልጾ እንመለከታለን፡፡ በመጨረሻ የሀገር ፍቅር ጀግንነት ሃያልነት መሰዋትነት በዚህ ጽሁፍ ተገልጿል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-** ኢትዮጵያ፣ አድዋ፣ የሀገር ፍቅር እና አብሮነት

## Abstract

*The principal aim of this paper was to analyse the major themes of the lyric of 'Adwa' by Ejigayehu Shebabaws', a prominent Ethiopian musician known for blending elements of nationalism, humanism, political and social activism in her lyric song. The paper focuses on understanding how Egigayhu's lyrics reflect themes of nationalism, humanism, patriotism, and the quest for unity, and equality within the Ethiopian context. The lyric recounts the significance of Adwa's victory over the invading Italian army and goes to the extent of asserting that Adwa is an identity of freedom. The paper also highlights Ejigayehu's role as a national figure and flag-waver whose music serves as a medium for expressing societal concerns and advocating for patriotism. Finally, the analysis of this paper elucidates the ways in which Ejigayehu's lyric song contributes to ongoing discourses surrounding Ethiopian identity, social healing, solidarity, dignity, and brevity of the society as the most recurring ones.*

**Keywords:** Ethiopia, Adwa, lyrics, patriotism, and solidarity

## 1. መግቢያ

ጥበብ ከሰዉ ልጅ ጥንተ ተፈጥሮ እና የህይወት መስተጋበር ላይ ያላት ጥብቅ ቁርኝት በቃላት በሚገለጽ እና ከባህር ቀለም ቢቀዳ በጽሁፍ ለመግለጽ በሚከብድ የሰሜት ልዕልት ነች። የሰዉ ልጅ ነጻ ፍቃድን፤ ምክኒያታዊነትን እና የተፈጥሮ ህግን በመጠቀም በእለት እንቅስቃሴዉ ከራሱ እና አካባቢያዊ ሥነ ምዳር እንዲሁም ከሌሎቹ ሰዎች ጋር በሚደረገዉ መስተጋብር ይጠበባል፤ ይቃኛል ይቀምራል ይመረምራል። እንደ ባዩልኝ አያሌዉ (2014) ገለጻ።

*Corresponding author: Daniel Mengistie, abush1978g@gmail.com Phone number: 251 912 186 204

DOI:
© 2022 Harla Journals and Author(s). Published by Dire Dawa University on Open Access Policy under CC-BY-NC 4.0.
Received: September 2024; Received in revised form: October 2024; Accepted: November 2024

የፎክሎር ምሁራን ክወናዊ ባህርይ ያላቸዉን ሥነ-ኪን ሀገረሰባዊ ትወን ጥበብ በማለት እንድ የፎክሎር ዘዉግ ያደርጉታል። ዶርሰንን(1972) ሀገራሳባዊ ትወን ጥበብ ሦስት ዘርፎች እንዳሉት አስቀምጧል። እነርሱም ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፤ ሀገረሰባዊ ዉዝዋዜ እና ሀገረሰባዊ ድራማ። ሙዚቃ የሰዉ ልጅ የግል እና የቡድን ፍላጎት፤ ሃሳብን፤ መከራን፤ ደስታን፤ ምኞትን፤ ከተፈጥሮ ጋር የለዉን መስተጋብር፤ እንዲሁም ረቂቁን አለም የሚጠየቅበት እና የሚገልጽበት ዘዴ እና መግበቢያ ነዉ።

ጋሻዉ አይፈራም (2012) ነጻነትን ጠቅሶ እንደገለዉ አሁን እስከ ደረሰንበት የእድገት ደረጃ ድረስ የሰዉ ልጅ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ ሙዚቃ ከፍተኛ አስተዋጾ አበርክቷል። ያለፈወን ታሪክ ለትዉልድ ለማስተላለፍ ሙዚቃ ጠቃሚ ነዉ። ሙዚቃ የአንድ ማህበረሰብን እሴት፣ ባህል፣ ልምድ እና ታሪክን በመግለጽ ማህበረሰብን ህልዉ ያደርጋል። ሙዚቃ የአንድ ማህበረሰብ መሰረት እና ሁለንተናዊ ነገር ነዉ። የአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ፣ ማንንት፣ ታሪክ እና ባህላዊ እሲቶችን፤ ጉዳዮችን እና ምንነት ያንጸባርቃል። የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ሥራ ውስጥ አስተሳሰባቸው፣ እይታዎች፣ መልክቶች፣ እየታዎች ታሪክ ትዉፊት ፍልስፍና ይንጸባረቃል። በገሀዱ አለም ዓለም የሚሰማዉን ስሜቶች ማለትም የሚያስደስተዊን ስኬቱን ድሉን፣ የሚቆጨቻቸው፣ ወይም በተቃራኒው የሚያስደስታቸው፣ የሚያዳጓቸው ደግሞም ቢሆን ብለው ቢሳካ ብለዉ ሚመኙትን እይታዎች በሚሰሮአዉ ስራዎች ዉስጥ ይገልጻሉ። ለህዝብም በተለያየ መንገድ እንዲረዳዉ መንገድ ያሳያሉ።

ደራሲያን በድርሰቶቻቸው ሁሉ ዉስጥ የሚያነሷቸው ሐሳቦች በሙሉ እውነተኛ እምነቶቻቸው ነጸብራቅ ነዉ ብሎ መደምደም ባይቻልም ነገር ግን ደጋግሞ ሊነሳ እና በአእምር የሚመላለስ የሐሳብ ክርክር እና ዉይይቶች ግን ይኖራሉ። ደራሲው ሆን ብሎም ይሁን ባጋጣሚ በልዩ ልዩ የጥበብ ቀለማት እና የእይታ ማዕዘን የገለጠው፣ የተመለከተዉ የነካካው፣ የተቸዉ የዘመረለት፣ ትኩረት ያደረገበት፣ ሀሳቡን መልክቱን፣ ፍልስፍናዉን እና ቁምነገር መተላለፉ ደራሲዉ ትኩረት የሚያደርግበት የሐሳቡ አቀንቃኝ መሆኑን ያሳያል። ሆኖም የአድናቆት ወይም የተቃውሞ፣ የፍቅር ወይም የጥላቻ፣ የናፍቆት ወይም የዝንጋኤ ክልል የደስታ ወይም የሀዘን ውስጥ ነው ብሎ ገቢራዊ ምልከታ ለመስጠት ወይንም ለማሔስ በርይከፍታል።

ደራሲው ደመ-ነፍሳዊ እሳቦት የተወለዱ ሐሳብቦችን፣ ገለጻዎችን፣ የቋንቋ አጠቃቀምን፣ አገላለጾች ፣ ትኩረቶች ላይ በጥልቅ ማጤን እና መገንዘብ ያስፈልጋል። ሆኖም አንዳንድ ግዜም ከዋናው ፈጠራ እና ከዋናዉ ጭብጡ ዉጭ በተጓዳኝ አቀራረቡ እና የተከተለዉ የጭብጥ ትንታኔዉ የደረሰበትን ድምዳሜውን ለማጠናከር የሚያግዙ ግብአቶች ይሆናሉ። አብዛኛውን ጊዜ የሚዘወተር ባይሆንም፤ የቀረበበት ቀን፣ በቀኑ የተከሰተ ኑባሬን በሚገባ በማጤን ለፍረጃ እና ለድምዳሜ የሚያበቃ ሰበብ ነው። ለምሳሌ ያ ህ ል የካቲት 23 ስንል መስከረም አንድ ስንል

ግንቦት 20 ስንል በአእምሮችን የሚመጡልን ስዕሎች የሚሰጡን ምልክቶች አሉ። ስለሆነም ከዚህ በመቀጠል የየካቲትን 23 ስለ ሚከበረዉ ታአላቅ የድል በአልን አያይዘን የአድዋ ድል በዘፈን ግጥም እንዴት ይታያል የሚለዉን እንመለከታለን።

የዚህ ጽሁፍ ርዕስ ‹ የእጅጋየሁ ሽባባዉ 'ትናገር አድዋ' የተሰኘዉ የሀገረ-ሰብ ዜማ ግጥም ትንታኔ › የሆነውም ለዚህ ነው። የእጅጋየሁ ስራ ትናገር ኢትዮጵያ በሚለዉ ምልኡ ስራዋ ለመተንተን ምቹ ናቸዉ። የግጥሙ ዉበት እና ፍሰት የሚነሳዉ ጭብጥየ ሀሳብ ጥልቀት የእይታዋ እና የምናባዊ ምጥቀቷ የቋንቋ አጠቃቀም ዉበት እጅ በአፍ የሚያስጭኑ የግጥሞቹ ስንኞች የሚጋልቡት የሀሳብ ይዘት እና ፍሰት የሰዉ ልጅ ለሀገሩ ያለዉን ጥልቅ ፍቅር የህዝብን አንድነት የሚያጸኑ መከባበርን በሸማ የሚለብሱ መዋደድን እንደ ገመድ የሚጋምዱ እና መከባበርን እነደ ጽጌረዳ አበባ የሚፈነድቁ ሆነዉ እናገኛቸዋለን።

በወቅቱ CNN ቴሌቪዥን ‹‹New talented Ethiopian singer Gigi›› ብሎ ሰፋ ያለ ዘገባ ሰርቶላታል። እጅጋየሁ እስካሁን ሰባት አልበሞችን ሰርታለች። ከአልበሞቹ መሐከል በኢትዮጵያ ውስጥ በይፋ የተከፋፈሉት ጉራማይሌ፣ እጅጋየሁ ሪሚክስ እና ሰምና ወርቅ የተሰኙት አልበሞች ናቸው። One Ethiopia ኢትዮጵያ ውስጥ ባይከፋፈልም በጎረቤት ሐገራት በኩል ገብቶ በስፋት የተደመጠ አልበሟ ነው። illuminated Audio (laswell's remix of the 2001 album 'Gigi') በ2003፣ Abyssinia infinite: Zion Roots, በ2003).

ከእለታት አንድ ቀን…ፕሮፌሰር ኃይሌ ገሪማ አድዋ ለተሰኘው ፊልማቸው ማጀቢያ ሙዚቃ ይሆን ዘንድ ማነው ለዚህ የተከበረየጥቁር ሕዝብ የነጻነት ተጋድሎ ፊልም ሙዚቃና ግጥም የሚጽፍልኝ ሲሉ በመላ አለም ማስታወቂያ ባስነገሩበት ወቅት አደዋን በኪናቸዉ ለማድመቅ በቁጥር የሚበዙ የጥበብ ሰዎች፡ ሁሉ ይህን ውድድር አሸንፎ ለአድዋ ጥሩ ማጀቢያ ሙዚቃ ለመስራት ይሯሯጥ ነበር። …ፕሮፌሰሩ እስካሁን ያሰቡትን ዐዓይነት ጎበዝ ባለቅኔ ድምጻዊ አላገኙምና ትተው ልሂድ ወስጣቸዉን በያዳምጡበት ወቅት እና የቀረችዋን ልጅ አድምጨ ልጨርስ እያሉ ማመንታት በጀመሩበት ስዓት…አንዲት ባገር ፍቅር ወኔ የተወሰወሰች ድምጸ መረዋ ወጣት ከተፍ አለች…ማር ወለላዋ፣ አፈ እርጎዋ፣ ዐይነ ሽልምልሟ፣ አዕምሮ ብሩኋኗ…እጅጋየሁ ሽባባዉ የተዘጋጀችዉን ድንቅ ዜማ በተዋቡ ግጥሞች አደዋን ተረከችዉ ደግሞም አዜመችዉ።

ፕሮፌሰሩ ብዕር በያዙበት እጃቸው ጉንጫቸውን ተደግፈው ካቀረቀሩበት አልተነሱም በምናብ ፈሰሱ ወደታሪክ አንጓዉ የሰዉነት ሚስጥር መደ ሆነዉ አድዋን እያጣጣሙ። እጅጋየሁ የአድዋ ጀግኖቿን በአዕይነ ህሊናዋ እየሳለችና ከውስጥ በሚፈልቀው ወኔዋ አለቅጥ እየጋለች በዛ ጥዕም ልሳኗ በቤቱ ውስጥ ያለውን ሰው ሁሉ ይዛው ወደ እናት ሐገር ኢትዮጵያ፤ አድዋ ትወነጨፍ በሀሳብ በአገሩ ሰማይ ላይ የሚበሩ በመንታ ዐይኖቹ ስቅስቅ ብሎ የሚያለቅስ እንጂ እንደሰው ተቀምጦ የሚያዳምጥ አንድም ነፍስ በስፍራው አልነበረም። ፕሮፌሰሩ ሲያነባ የቆየውን ዐይናቸውን ጠረግ አደረጉና ካቀረቀሩበት ቀና ብለው ጂጂን ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ጸጉሯ ተመለከቷት። (ይሄኔ ይበልጥ ፈራሁዋቸው

ትላለች ጂጂ) ዐይናቸውን አሸት አሸት እያደረጉ “ነይስኪ ወደኔ” አሏት ጂጂም ትንፍሽ ሳትል ካጠገባቸው ተቀመጠች፡ ፡ “በይ እናቴ ከእኔም ግምት በላይ ሆነሽ ሰርተሽዋል የአድዋ ድልን ከኛ በላይ የተረዳሽው አንቺው ነሽ በቃ መርጬሻለሁ ነገውኑ ተመልሰሽ ነይ።” እያሉ ስራዋን እንደወደዱላትና የፊልሙ ማጀቢያ ሙዚቃ ለማድረግ እንደወሰኑ አበሰሯት። (በሸገር FM 102.1 ለመአዛ ብሩ ቃለ መጠየቅ)።

## 2. የጽሁፍ መነሻ ምክኒያት

በሙዚቃ ግጥም ዉስጥ የጥበብ ሰዎ ስለ አድዋ ታላቅነት በዜማቸዉ የገለጡበት ሁኔታ እና የተተነተኑበት መንገድ ብዙም አይደለም። ስለሆነም የእጅጋየሁ ሽባባዉ ትናገር አድዋ የተሰኘዉ ለፊልም ማጀቢያነት ተብሎ የተሰራዉ ድንቅ ስራ በመቅረጸ ድምጽ በትእይንተ መስኮት አንዳንድ መሀራን የራሳቸዉን እየታ እና ትንታኔ አቅርበዋል። እኔም ይህ ድንቅ ስራ ከማህበራዊ ፋይዳዉ እና የግጥሞቹን ጭብጥ ለመተንተን ሞክሪያለሁ።

## 3. ጥናቱ ስነ ዘዴ

በዚህ ጥሁፍ ተግባራዊ ከተደረጉት የጥበብ ጽሁፍ ተግባራዊ ከተደረጉበት የጥናት መረጃዎቹ ከሚተነትኑበት መንገድ አንጻር የዓይነትዊ አንጻብ የምርምር ስልት ተጠቅሚያለሁ። የዘፈኑን ግጥም ሁለንተናዊ የፋይዳ እና ጭብጣዊ የትንተና መንገዶች የአተናተን ጎዳና በመከተል ነዉ።

## 4. የእጅጋየሁ ሽባባዉ ‘ትናገር አድዋ’ የተሰኘዉ የሀገረ-ሰብ ዜማ ግጥም ትንታኔ

የእጅጋየሁ ሐገራዊአጀንዳዎችን በዘፈን ግጥሞቾ ስታነሳ ሐሳቧ ይሰላል ቋንቋና ዘይቤዋም እንደ ወንእ ጅረት ያለማቋረጥ ይፈሳል። ብዙ የስነ ጽሁፎች ሰዎች ስለ እጅጋየሁ ሲነገሩ ኢትዮጵያዊነትን በእዉነተኛ ገለጻ የምታስተጋባ አርቲስት የሚል ድምዳሜ ላይ ካደረሱን ምክንያቶች መሐከልም አንዱ እይታዋና ጥልቅ ምልክታዎች እና ሀገሮን የምታይበት ፍልስፍና ዋነኛዉ ይህ ነው። ሐሳቦች አለማቀፋዊ እዉነታዊችን የሚዳስሱ ናቸው፡ ፍቅር፣ ረሀብ፣ ጥጋብ፣ ንዴት . . . በሁሉም የዓለም ክፍል ላይ አሉ። እነኝህ ደግሞ የሰው ልጅ ባለበት አጽናፍ ዓለም ሁሉ ይገኛሉ። በዘፈን ግጥሞቿ ላይ የተነሱ ሐሳቦች ኢትዮጵያዊነትን ከድል አድራጊነት እና ሀያልነት አንጣር የሚዳስሱ ናቸዉ በተለይ አድዋን በተዋበ ዜማ እና በተከሸኑ የግጥም ቃላት ቀለም ትቀበዋለች።

**"ትናገር አድዋ"**

**———————**

- **አድዋ ማን ነች?**
- **አድዋ ለምን በአንስታይ ጾታ ተጠቀመች ኪያኔዋ?**
- **አድዋ የማን ለማን ነው?**

አድዋ ከያኔዋ በሴት ጾታ የተጠቀመችዉ ሴት ልጅ ለነጻነተዋ ያላትን ቁርጠኝነት የሚገልጽ እና ለነጻነት የሚታገሉ በነጻ ሀሳብ ወደ አለማት ህያዉ ፍጡርን የማምጫ መንገድ ሥለሆነች ጭምር ነዉ። ጂጂ ትናገር ዐድዋ ስትል እራሳዋም

አንስታይ በመሆነዋ እና በዋናነት የጦሩ ኦፕሬሽን የተነደፈዉ ድግሞም ድልን ያጣጠሙት የሴቶች ሃያልነት የጥበበብ ሃይል ያሳየችዉ ዕቴጌ ጣይቱ ሴት ስለነበሩ ነዉ።

«ስለ አድዋ ድል ከመናገራችን በፊት ዓድዋ ድል እንዲሆን አልያም የዓድዋ ጦርነት እንዲመጣ ቅድመ ነገሮች ብዙ ናቸዉ። ዓድዋ በራሱ እንደ ጦርነት ሆኖ አልመጣም። የአዉሮጳ ሃያላን መንግሥታት በተለይ አፍሪቃን በተለያዩ የራሳቸዉ የቅኝ ግዛት ክልሎች ዉስጥ ለማዋል፤ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል በዚህም ተስመማምተዋል ። አፍሪቃ ዉስጥ የየራሳቸዉን ድርሻ ተከፋፍለዋል። ይህ ከመሆኑ አስቀድሞ ግን የስዊዝ በይ መከፈት እንዲሁም በቀይ ባህርና አካባቢዉ ጆኦ ፖለቲካ ቀይ ባህርን የመቆጣጠርያ ፤ የአባይን ምንጭ የመቆጣጠር ሂደት ዉስጥ ተደጋጋሚ ጦርነቶች ኢትዮጵያ አካናዉናለች። ከነዚህም አንዱ ከአድዋ ጦርነት በፊት የተደረገዉ የጉራ የጉንደት እንዲሁም ደግሞ ከጣልያን ጋር በሰሃጢና በዶጋሊ የተደረገዉ ጦርነት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ። »

‹‹በ20ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ትኩረትና ፊቱን ኢትዮጵያ ላይ እንዲያደርግ ካስገደዱት ጥቂት ክስተቶች መካከል አንዱና ዋናው የዓድዋ ድል ነው›› በማለት ታዋቂው የታሪክ ሊቅ ባህሩ ዘውዴ መናገራቸዉ ድርሳናት ይናገራሉ። በዝያን ጊዜ የቅኝ ግዛቶች ቀደዉ ያወጥዋቸዉ አዲስ አካባቢዎች ይላሉ ፤ አቶ ኃይለ መለኮት አግዘዉ በመቀጠል በኢትዮጵያ ላይ ለተከሰቱ በርካታ ጦርነቶች መንሲኤ ለመሆን በቅተዋልም ይላሉ። አድዋ ከዝያ በኋላ ለነበረዉ አርበኝነት መሠረት የጣለ ድልም ነዉ ሲሉ አቶ ኃይለመለኮት ሀሳብ ይጨምራሉ። (Äthiopien Addis Abeba Annual national celebrations Adwa Victoy).

«በ1879 የዶጋሊ ጦርነት ተደርጎ ጣልያኖችን ባናስወጣም ዶጋሊ የራስ አሉላን ታላቅነት ያስመሰከረና ፤ ለቅኝ ግዛት አንበረከክም የሚለዉን ያሳየ ነበር። ከዝያ በመቀጠል የነበረዉ ከክዋት ጦርነት የምንለዉ ራስ መንገሻ በኢጣልያኖች ድል የተደረጉበት ጦርነት ነዉ። በኋላም ከአጼ ምኒሊክ ጋር ዉጫሌ ላይ በተደረገዉ ዉል፤ አንቀጽ 17 ኢትዮጵያ በጣልያን ሥር እንደሆነች የሚያሳየዉ ዉል ወደ ጦርነት እንድናመራ ተደርጎአል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ጦር ከአዲስ አበባ እስከ ዓድዋ 1066 ኪሎ ሜትር በመጓዝ የኢጣልያን የተቀረዉን የኢትዮጵያን ክፍል የመያዝ ህልም አክሽፎአል። ያ ማለት በተቀሩት አንዳንድ በታዎች በምስራቅም ይሁን በሰሜን ኢትዮጵያ የቅኝ ግዛቶች ቀደዉ ያወጥዋቸዉ ግዛቶች ተፈጥረዋል።

መረማመጃም ሆነዉ በኋላ ላይ ኢትዮጵያ ላይ ለተከሰቱ ብዙ ጦርነቶች፤ እንዲሁም አሁን ላይ ላሉት አንዳንድ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮች መንስዔ ሆንዋል። ነገር ግን ዓድዋ ለኢትዮጵያዉያን ከዝያ በኋላ ለነበረዉም አርበኝነት መሠረት የጣለ ድል ነዉ። የዓድዋ ተራሮች «ማዉንቴን ኮንፈረንስ» ይባላሉ ፤ አካባቢዉ ላያ በትግርኛ አጽበ ጽዮን ይባላሉ፤ የጽዮን ጠባቂ የሚባሉተራሮች ናቸዉ ኋላ ላይ ታላቁ የዓድዋ ድል መሠረት የሆኑት።

ለዚህም ዓድዋ በጦርነቱ ብቻ አይደለም የሚታወቀዉ እንደርታን የሃን እና የመሳሰሉትን የዚያ አካባቢ ቦታዎችን ይዞ በዝያ መስመር ያለ ትልቅ የኢትዮጵያ ስልጣኔ መሰረት የሆነም ስፍራ ነዉ። ዓድዋ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ብዙ ብዙ አበርክቶ ያለዉ አካባቢ ነዉ።

**የሰው ልጅ ክቡር**

**ሰው መሆን ክቡር**

**ሰው ሞቶል ሰው ሊያድንሰውን ሊያከብር**

አድዋ ኢትዮጵያኖች ናቸዉ። ለእኔ፣ ለወገኖቻቸዉ የሞቱት የታረዱት ብዙ ነገር የሆኑ ለሀገር የተበረከተ ጽዋ ነዉ። ክቡር የሆነዉን የሰዉን ልጅ በእኩልነት በማያዩ ተፈጥሮ የሰጠችንን ነጻነት ሊቀሙን እነሱ ወደኛ ሃገር መጡብን እንጂ እኛ አልሄድንባቸዉም። ይሄ የጀግንነት ብቻ ታሪክ አይደለም የሰዉ ልጅ ታሪክ እንጂ ! ” አዎ አድዋ የሰው ልጅ ሁሉ ታሪክ ነው። የእጅጋየሁ ሽባባው(ጂጂ) አድዋ፣ በመንፈስ ወደ ሁላ ወደ ጥንት ተጉዞ፤ የሰው ልጅ ‶ሀ″ ብሎ ሲፈጠር ከተሰጠው ጸጋና ክብር ይጀምራል። ‶የሰው ልጅ ክቡር፤ ሰው መሆን ክቡር…″ መጸሀፍ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌችን እንፍጠር ያለዉ ቃል የተፈጸመበትን ቃል በተከሸነ ቃላት የተገለጸበት ነዉ። ጂጂ አድዋን፣ ‶የሰው ልጅ ክቡር፣ ሰው መሆን ክቡር″ ብላ ህያዉነትን በሚገልጸዉ የተከሸኑ ቃላት እና የተዋበ ዜማዋን አሃዱ ብላ የጀመረችዉ የሁሉ ስነ ፍጥረት አዉራ የሰዉ ልጅ ክብር ነዉ። የሰዉ ልጅ ክብርን የጀመረችበት መንገድ ታሪክ-አድዋን ያየችበት፣ ሀቁን የተገነዘበችበት እና እንዲተኮር የፈለገችው የሰዋዊ ክብርን ነው።

የሰው ልጅ ትልቁ ጸጋ፣ ሰው ሆኖ የመፈጠር፣ ተፈጥሮም በክብር የመኖር ጸጋ በአድዋ ውስጥ ስትገልጥ እናያለን። «121ኛው» የዓድዋ ድል ክብረ በዓል ከሶሎዳ ተራራ ግርጌ ያከበሩት የአድዋ ክብረ በአል ላይ የተጋበዙት የቀድሞዉ የደቡብ አፍሪቃ ፕሬዚዳንት ታምቦ ኢምቤኪ በአድዋ ከተማ ላይ በተከበረዉ ደማቅ ዝግጅት ላይ ተገኝተዉ «የአድዋ ድል በዓልን የመላው አፍሪቃ ሀገራት በዓል ማድረግ ይቻላል» ብለዋል ይህ ማለት የሰዉ ልጆች ሞት ለፍትህ ለነጻነት ለሁሉ የተከፈለ ደግሞም ለሰዉ ልጆች ክብር መሆኑን በሚገባ ይገልጽልናል። በመቀጠል ጂጂ…

**በደግነት በፍቅር በክብር ተጠርቶ**

**በክብር ይሄዳል ሰው ሊኖር ሰው ሞቶ**

የሰዉ ልጅ ለሞት በክብር የተጠራበትን የንጉሱን የክብር ጥሪ የተቀበለበት ነዉ። ከያኒዋ በስራዋ የንጉሱን አዋጅ የክብር ጥሪ መሆኑን እና ለቤዛነት የሰዉ ልጅ ወደ ሞት የሄደበትን መንገድ ትገልጻለች። አዋጅ ሰምቶ የተመመዉን ሰዉ ህያዉነትን በማያያዝ "አንዱ ስለ ሁሉ ቤዛ ሆነ ያለዉን " የሰው ልጅ ከተሰጠው ክብር አንሶ ሲወርድ፣ ረክሶ ግን ለዘለአለም እንዳይኖር፣ ክርስቶስ ለሰው ልጆች መድህን ይሆን ዘንድ፣ የቅዱስ መጸሀፍ ቃል ክርስቶስ ለሰው ልጆች መድህን ይሆን ዘንድ፣ ለሌሎች ምሳሌነትን የገለጸበት ስዕል በሚገባ አድዋን ገልጻበታለች።

ይህንን ለሰው ልጅ ቤዛ የመሆንን አስተምህሮት፤ ለሰው መሞት፣ ለሰው ክብር መሰዋት፤ ከምንም በላይ ሰው ክብር መሆኑን በመገንዘብ በአድዋ ተራራ ״ በክብር ይሄዳል፣ ሰው ሊኖር ሰው ሞቶ...״ በማለት በአድዋ አባቶቻችን መተኪያ የሌላትን አንድያ ትልቁ የፍቅር መገለጫ የሆነዉን ነፍሳቸዉን መስጠታቸዉን ጂጂ በሙዚቃው ወስጥ ጀግኖች አባቶቻቻን ሰው ልጅ ክብር፣ ሰው መሆን ክቡር መሆኑን ተገንዝበውና አስገንዝበው እንዳለፉ በሰሉ ግጥሞቸዋ ለትዉልድ ታስረዳለች።

**የተሰጠኝ ህይወት ዛሬ በነፃነት**

**ሰው ተከፍሎበታል ከደም እና ከኣጥንት**

ከዚህ ስንኝ የምንረዳዉ በአለም ላይ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በነጻ የበታችነት ስሜት ሳይሰማዉ በነጻ ይራመድ ዘንድ የአያቶቹ ደም ፈሶለታል እንደ ጅረት። ደግምም የስጋቸዉ ማወዳጃ አጥንታቸዉ ተከስክሶለታል ማለት ነዉ። ነጻነት ዝንብሎ በነጻ የሚታደል ስጦታ አይደለም ዉድ የሆነዉን በአምሳለ ዐማልክት የተፈጠረውን ምድርን የሚገዛዉን የሰዉ ልጅ ህይወት የሚነጥቅ ግን ትርፉ ለሌላዉ በነጻነት ይኖር ዘንድ ሞትን ንቆ የሞትን ጽዋውን መጎንጨት ነዉ። ተምሳሌትነቱ ክርስቶሳዊ፤ አድርጋ አባቶቻችን የህይወት፣ የመዳን፣ የፈውስ፣ የቤዛ ምልክቶች ናቸው ልትለን እና አድዋን አግዘፍ ልትሰጠው ስትፈልግ ״ሰው

ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት...״ ስትለንም ጂጂ የሰዉ ልጅ በክብር እራሱን ለመሰዋትነት ያበቃዉ፤ ወራሪን ለመመከት፣ አገር ለመስራት፣ ቅኝ ግዛትን ለማውገዝ ወዘተ ለሚባል የታሪካችን ክፍል ሳይሆን ከዚህ ያለፈ በዘላለመዊነት አምላክ ሀሳቡ የሰዉ ልጅ በመንፈስም በስጋም ነጻ ይሆን ዘንድ ነጻ እደሆነ ትገልጻለች።

**ስንት ወገን ወደቀ በነፃነት ምድር**

**ትናገር አድዋ ትናገር ትመስክር**

**ትናገር አድዋ ትናገር አገሬ**

**እንዴት እንደቆምኩኝ ከፊታቹ ዛሬ**

ከላይ በተቀመጠዉ ግጥም ባለ ቅኔዋ በቃላት የማይገለጽ ዋጋ መከፈሉን ታሪክን ትገልጣለች። አጤ ሚኒሊክ በጳዉሎስ ኞኞ መጸሀፍ ምን ያህል አባቶች እነደደከሙ ታሪክ እንደሰሩ ይገልጻል። ምኒልክ የጦርነቱን ክተት አውጀው ከአዲስ አበባ የተነሱት ጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም ነበር። ኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም አምባላጌ ላይ፣ ታኅሳስ 1888 ዓ.ም መቀሌ ላይ በተደረገውዘመቻ ድል ተቀዳጅተዋል። ከዚያ በኋላ የፍልሚያው ሥፍራ ዓድዋ ላይ የነበረ ሲሆን፣ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ያዘመቱት

ጦር ቁጥር ግን በልዩ ልዩ ጸሐፊዎች የተሰላው በተለያየ ቁጥር ነው። የኢንጂነር ካፑዚ ግምት- 85 ሺሕ ባለጠመንጃ ሲገመት ፤ በአድዋ ጦርነት ላይ በኢትዮጵያ ወታደሮች ከተማረኩና ከተያዙ በኋላ ነፃነቱን አግኝቶ ኢጣሊያ የተመለሰው

የጄኔራል አልቤሮቶኒ ግምት ኢትዮጵያ ከ111 ሺሕ እስከ 122 ሺሕ ያህል ወታደሮች እንዳሰለፈች በታሪክ ማዛግብቱ ላይ ተይቦታል። የሰዉ ልጅ በሰዎች መካከል ሲቆም በክብር የነጻነቱ ዋጋ መሆኑን አጽንኦት ትሰጣለች እና አኣለም ላይ በሰወች ፊትበድፍረት የመትኮራበት መሆኑን ጂጂ በተወደደ ግጥሟ ትገልጻለች።

**በኩራትበክብር**

**በደስታበፍቅር**

አባቶቻችን ነጻነትን ያጎናጸፋን ነጻነት ሰው ሆኖ ከመፈጠር ጋር የሚሰጥ እንጅ የማንም ችሮታን እንደማይጠይቅ፣ ጥንት አባቶቻቻን ቀድመዉ ስለተረዱት እሰከ ሞት ድረስ ዋጋ ከፍለዋል። በጂጂ በሙዚቃዋ ውስጥ የነጻነት ዋናዉ ትርጉም ደግሞ ምንጩ የሰው ልጅ ክቡር እንደሆነ በሚገባ መረዳት እንዳለብን ትነግረናለች። በብርቱ ዋጋ የተገኘዉን እንዴት ሀሴት እንደምታደርግበት እንዲህ በማለት ″በኩራት፣ በክብር፣ በደስታ፣ በፍቅር፤ በድል እኖራለሁ ይኸው በቀን በቀን…″ እያለች ታሸሞነሙናለች የነፃነት ምንጭ የሆነውን የአድዋን ቱርፋት።

**በድል እኖራለው ይኅው በቀን በቀን**

**ደሞ መከራውን ያን ሁሉ ሰቀቀን።**

የእጅጋየሁ ሽባባው አድዋ የትላንት በፊትን ታሪክ ብቻ አይደለም፣ እለት በለት የምንኖረዉ የምናስበዉ፤ ምናሰላስለዉ እና ያገኘነዉን የነጻነት ቀነዲል በድል አድራጊነት መንፈስ እነደምትኖረዉ እናም እኛም ከዚህ የ አባቶቻችን በረከት በቀን በቀን እነድናጣጥመዉ በሙዚቃዋ ትመክረናለች። በመቀጠል "ደሞ መከራውን ያን ሁሉ ሰቀቀን " ስትል ነጻነቱን ብቻ ሳይሆን ጂጂ በቁጭት አባቶች የከፈሉትን መከራ አድዋ ላይ አይተኬ ህይወታቸውን ለሰው ልጅ ክብር የሰጡበትን መንገድ አድንቃ፣ ″ሰው መሆን ክቡር″ እንደሆነ ያሳዩንን የጀግኖች አባቶቻችን ገድል ሠዎች እንዲረዱት አጥንት እና ጅማትን ሰብሮ በሚገባ ቃላት ትናገራለች።

**አድዋ ዛሬናት አድዋ ትናንት**

**መቼ ተነሱና የወዳደቁት**

**ምስጋና ለነሱ ለአድዋ ጀግኖች**

**ለዛሬ ነፃነት ላበቁኝ ወገኖች**

በጂጂ ″አድዋ ዛሬ ናት አድዋ ትላንት፤ መቸ ተነሱና የወዳደቁት…″ ስትል የአድዋ ቱርፋቶች የትላንት ብቻ እናዳልሆኑ በሚገባ ትገልጻለች በመቀጠል እነኛ ዋጋ የከፈሉልን ሳይነሱ ለክብር ከወደቁበት ለምን እኛ በአሸነፍነዉ ነገር እናደወድቅን በምጸት ትገልጻለች። የአድዋ ጀግኖች አባቶቻቻን በክብር አላረፉም። የወዳደቁት የሚነሱት እኛ እነርሱ የከፈሉልንን መስዋት የሚመጥን ስራ ለሀገር አለመስራታችን እና የአባቶችን አደራ በክብር የማይጠብቁ ልጆች ባለመገኘቱ ቁጭቷን ይታያል። በጂጂ በተጨማሪም ″አድዋ″ የተሰዉት ጀግኖች አባቶቻቻን በሰላም አላረፉም። በየጥሻው እንደወዳደቁ መቅረት ለጂጂ ጸጸት እንደሆነባት ግልጽ ነው።

ጂጂ ˝መቸ ተነሱና የወዳደቁት˝ ስትል ትላንት ሰው የሚባል አርማ አንስተው፣ ሰው በሚባል የወል ስም ለሰው የሞቱ አባቶች በኖሩባት አገር፣ ዛሬ ˝አድዋ ላይ የአድዋ ጀግኖችን በሚያሳፍር ሁኔታ የቀበለያቸዉ፤ የብሄሩ ጀግና ለያደርጉቻዉ የሚፈልጉትን ስታይ ጂጂ ˝አድዋ ዛሬ ናት አድዋ ትላንት፤ መቼ ተነሱና የወዳደቁት…˝ ብትል፤ አብዝታም ብትቆጭ የሚጨበጥ አመክንዮ ስላላት ነዉ፡፡

**የ ጥቁር ድል አምባ አድዋ**

**አፍሪካ እምዬ ኢትዮጵያ**

**ተናገሪ ተናገሪ**

**የድል ታሪክሽን አውሪ**

**እእእእ ተናገሪ..**

ዓድዋ፡ የቅኝ ግዛት ዘመን ትርክትን የቀየረ ገድል በካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በአጼ ምኒልክ በተመራው የኢትዮጵያ ሠራዊትና ባህር አቋርጦ ከአውሮፓ ከመጣው የጣሊያን ሠራዊት ጋር የተካሄደው የዓድዋው ጦርነት በታሪክ ውስጥ ከሚጠቀሱ ጉልህ ክስተቶች መካከል አንዱ ነው። የኢትዮጵያ አርበኞች የዓድዋ ድል ጣሊያን አፍረካ ውስጥ በተለይ ደግሞ በምሥራቁ የአህጉሪቱ አካባቢ ለማስፋፋት አቅዳ የተነሳችለትን የቅኝ ግዛት ዕቅድን ያጨናገፈ ከመሆኑ ባሻገር፤ በዘመኑ የአውሮፓዊያን ሠራዊት በአፍሪካዊያን ካበድ ሽንፈት ሲገጥመው የመጀመሪያ በመሆኑ ድንጋጤንም ፈጥሮ ነበር።

የዓድዋ ጦርነት ድል ለጣሊያኖች ሽንፈት አስከትሎ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ከማጽናት ባሻገር ከአድማስ ተሻግሮ አህጉራትን አቋርጦ የተሰማ ጉልህ ተጽዕኖን በዓለም ዙሪያ አስከትሏል። በዘመናዊው ዓለም የጸረ ቅኝ ግዛት ትግል ውስጥ የኢትዮጵያ ስም ተደጋግሞ ከሚነሳባቸው ክስተቶች መካከል አንዱ ለመሆን ከመብቃቱ ባሻገር በተለይ ደግሞ በጥቁሮች ዘንድ የዓድዋ ድል ለነጻነት በሚያደርጉት ትግል ውስጥ መነቃቃትንና ተስፋን የሰጠ ክስተት ሆኗል። የዓድዋ ድልን ተከትሎ የታዩ ክስተቶችን በመመልከት የተለያዩ የታሪክ አጥኚዎች የኢትዮጵያዊያን ድል ያስከተለው ውጤት በሚል የሚከተሉትን ነጥቦች አስፍረዋል።

አፍሪካን ተቀራምተዋት በነበሩት ቅኝ ገዢዎች ላይ ስጋት ፈጠረ። ዓድዋ አፍሪካ ውስጥ አውሮፓዊያንን የሚገዳደር ወታደራዊ ኃይል እንዳለ አሳይቷል። ነጮች በጥቁሮች ላይ የነበራቸውን የኃያልነት ትርክት ከመሰረቱ ቀይሯል። ዓድዋ ኢትዮጵያ ለጥቁሮችየነጻነት ቀንዲል ሆና እንድትታይ አድርጓታል። የጣሊያንን መስፋፋት ቀያሽ የነበረው ፍራንሲስኮ ክርስፒ አስተዳደር እንዲወድቅ ምክንያት ሆኗል።

የዓድዋን ጦርነትን የመራው የታላቁን ጀነራል ባራቲየሪ ውድቀት ሆኖ ለሽንፈቱ ክስ ተመስርቶበት ነበር። በመጨረሻም የዓድዋ ጦርነት ምክንያት የነበረውን የውጫሌ ስምምነትን ውድቅ የሚያደርገውና የኢትዮጵያን ነጻ አገርነት የሚቀበለውን የአዲስ አበባ ስምምነትን ጣሊያን እንድትፈርም አደርጓል። ለዘህም ነዉ የነጮችን አሸናፊነትን የሰበረ የጥቁር ድል አንባ

አድዋ የበራላት ከያኒዋ ዋላቷን የሰደረችዉ።

በመጨረሻም ጂጂ ታመላክታለች ″ተናገሪ″ ትላላች፤ አድዋ አፍ ያለት ይመስል። ″ተናገሪ″ሀገሬ ትላላች፣ አገር ያልታዘበችይመስል። ትናገር ትላለች ትውልድ ጆር ስጥቷት ይሆን? የምትናገረዉንስ የዘመኑ ሰዉ ሰምቶ መልስ የሰጣት ይሆን? የድል ታሪኳን የሰማት ይኖር? ዛሬም የእኔም ጥያቄ ነዉ።

## 2. ማጠቃለያ

ሙዚቃ የአንድ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ነገር ነዉ። የአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ እሲቶችን፤ ጉዳዮችን እና ምንነት ያንጸባርቃል። የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ሥራ ውስጥ አስተሳሰባቸው ይንጸባረቃል። ጂጂ "ትናገር አድዋ" የጥቁር ሕዝብ የነጻነት ተጋድሎ ፊልም የማጀቢያ ሙዚቃ ላይ ዐድዋን ከጦርነት ማሸነፍ በላይ የሰዉ ልጅ በነጻነት በህያዉነት ይኖር ዘንድ ዋጋ የተከፈለ መሆኑን በተዋበ ቃላት ትገልጻለች። አድዋ ኢትዮጵያኖች ናቸዉ፡፡ ኢትዮጵያኖች ማለት ነጻ ሰዉ ማለት ነዉ። አድዋ የጀግንነት ብቻ ታሪክ አይደለም የሰዉ ልጅ ታሪክ እንጂ። አድዋ የሰው ልጅ ሁሉ ታሪክ ነው።

ጂጂ አድዋን፣ ″የሰው ልጅ ክቡር፣ ሰው መሆን ክቡር″ ብላ ህያዉነትን በመግለጽ የሰው ልጅ ትልቁ ጸጋ፣ ሰው ሆኖ የመፈጠር፣ ተፈጥሮም በክብር የመኖር ጸጋ በአድዋ ውስጥ ስትገልጥ እናያለን። «አድዋ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመላው የጥቁር ሕዝብ ድል ነው። የዓለም ጥቁሮች ሲያከብሩት እኛ ልንኮራበት እንጂ ልንወዛገብበት አይገባም። በጂጂ ሙዚቃዋ ውስጥ የጻነት ዋናዉትርጉም ደግሞ ምንጩ የሰው ልጅ ክቡር እንደሆነ መረዳትና እንዳለብን ትነግረናለች፡፡ በብርቱ ዋጋ የተገኘዉን እንዴት ማጣጣም እንዳለብን እና የተከፈለዉን ዋጋ እንድንረዳዉ ታሪኩንም ለትዉልድ ልናስተላልፈዉ እነደሚገባ ታሳስባለች። አጠቃላይ አድዋ ሰዉ ለሰዉ በሰዉ የተከፈለ የነጻነት ህላዊ ነዉ።

### ማጣቀሻ መፅሀፍት


ባዩንኝ አያሌዉ (30 2014) "ኪነ-ጥበብ" በአማርኛ ሥነ-ግጥም።በሸገር FM 102.1 ለመአዛ ብሩ ቃለ መጠይቅ

ተስፋዬ እሸቱ (2001) የእጅጋየሁ ሽባባው (ጂጂ) ሰርክ ገዝፎ የሚንጥ፣ እሩቅ ግን ቅርብ ውብ ስሜት.... አድዋ።ነጻነት

መሰረት (2007) ባህልና ሙዚቃ ። ናይል 5ኛ ዓመት ቁጥር 02

ዘመን እና ጥበብ መጽሔት ጥቅምት 2010ዓ.ም እትም።ጳዉሎስ ኞኞ (1984) አጤ ሚኒሊክ።

Dorson, R. (1972). Folklore and Folklore Life: An Introduction. Chicago: The University of Chicago.

Äthiopien (2010) Addis Abeba Annual national celebrations Adwa Victoy

'The Ethiopian Herald' ጋዜጣ April 26/1996 እንዲሁም 'አዲስ ትሪቡን' ግንቦት 4/1988ዓ.ም።

Illuminated Audio (laswell's remix of the 2001 album 'Gigi') በ2003፣ Abyssinia infinite: ZionRoots.

Harla Journal of Social and Behavioral Studies gives access to this work open access and licensed under a Creative Commons Attribution-NonCommercial 4.0 International License. (Creative Commons Attribution-NonCommercial 4.0 International License)